# ሮቸየዘርፍ፣ የሙያ ማኅበራት እና የዘርፍ ማኅበራት ምክር ቤት አደረጃጀት፣ ድጋፍ አሰጣጥና ክትትል መመሪያ ቁጥር 548/2013

የዘርፍና የሙያ ማኅበራትን በየዘርፉ ለራሳቸውና ለሃገራቸው የኢኮኖሚ እድገት ሊያስገኙ የሚችሉበትን ሁኔታ የበለጠ ለማጎልበት፣ ለማስፋፋትና ለማጠናከር በማስፈለጉ፣

የዘርፍ፣ የሙያ ማኅበራቱ እና የዘርፍ ማኅበራት ምክር ቤቶቹ የአምራች ኢንዱስትሪዎችን ድምፅ በተለያዩ መድረኮች ላይ በአጥጋቢ ሁኔታ ማቅረብ እንዲችሉ ማመቻቸት በማስፈለጉ፣

ለዘርፍ፣ ለሙያ ማኅበራቱ እና ለዘርፍ ማኅበራት ምክር ቤቶቹ ድጋፍ የሚሰጥ የሚከታተልና የሚኒስቴሩ እና በተዋረድ የክልልና የወረዳ የሥራ ኃላፊነት መለየትና ማመልከት በማስፈለጉ፣

በሥራ ላይ ያለውን የዘርፍና የሙያ ማኅበራትን አደረጃጀት፣ ክትልልና ድጋፍ አሰጣጥ መመሪያ ማሻሻል አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፣

የኢንዱስትሪ ሚኒስቴር የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፑብሊክ አስፈፃሚ አካላትን ሥልጣንና ተግባር ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር 691/2003 አንቀጽ 20/1/ሰ እና የንግድና የዘርፍ ማህበራት ምክር ቤቶች ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 341/1995 አንቀጽ 35 መሠረት ይህን መመሪያ አውጥቷል፡፡

## ክፍል አንድ
## ጠቅላላ

### 1. አጭር ርዕስ

ይህ መመሪያ የዘርፍ፣ የሙያ ማኅበራት እና የዘርፍ ማኅበራት ምክር ቤት አደረጃጀት፣ ድጋፍ አሰጣጥና ክትትል መመሪያ ቁጥር 548/2013 ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

### 2. ትርጓሜ

በዚህ መመሪያ ውስጥ የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር ፡-

1. “ሚኒስቴር” ማለት የኢንዱስትሪ ሚኒስቴር ነው፡፡
2. “የሙያ ማህበር” ማለት ትርፍ ለማግኘት ወይም ለመከፋፈል ሳይሆን በአምራች ዘርፍ በፈቃደኝነት ላይ በመመሥረት አንድን ሙያ ለማስፋፋት፣ በሙያው የተሠማሩ ግለሰቦችን ፍላጎት እንዲሁም የኀብረተሰቡን ፍላጎት ለመወከል በሙያ ዘርፉ ሙያተኞች የተደራጀ ማኅበር ነው፡፡

3. “በኢንዱስትሪ ዘርፍ ያሉ ጥቃቅን የሥራ ድርጅቶች” (መፈብረክ፣ ግንባታ፣ ማዕድንና የግብርና ምርት ማምረት) ማለት ባለቤቱን ጨምሮ በ5 ሰዎች የሚንቀሳቀስ እና ጠቅላላ ድምሩ ከብር100,000 ያልበለጠ ንብረት የያዘ የሥራ ድርጅት ነው፡፡

4. “በኢንዱስትሪ ዘርፍ ያለ አነስተኛ የሥራ ድርጅት” (መፈብረክ፣ ግንባታ፣ ማዕድንና የግብርና ምርት ማምረት) ማለት ከ6 — 30 በሚሆኑ ሰዎች የሚንቀሳቀስና ጠቅላላ የተከፈለ ካፒታል ከብር100,000 በላይና ከ1.5 ሚሊዮን ብር የማይበልጥ ንብረት ያለው የሥራ ድርጅት ነው፡፡

5. “መካከለኛ የማኑፋክቸርንግ ድርጅት” ማለት ከ31- 100 በላይ የሆኑ ሰዎችን የቀጠረና ካፒታሉ ከብር20 ሚሊዮን ንብረት የማይበልጥ ንብረት ያለው እና በኃይል ምንጭ በሚንቀሳቀስ ማሽን የሚጠቀም የሥራ ድርጅት ነው፡፡

6. “ከፍተኛ የማኑፋክቸሪንግ ድርጅት” ማለት ከ101 እና ከዚያ በላይ የሆኑ ሰዎችን የቀጠረና ካፒታል ከብር20 ሚሊዮንና ከዚያ በላይ ንብረት ያለውና በኃይል ምንጭ በሚንቀሳቀስ ማሽን የሚጠቀም የሥራ ድርጅት ነው፡፡

7. “ባለ ብዙ ማህበር” ማለት በተለያዩ ዘርፎች እና/ወይም ሙያዎች የሚገኙ ሆነው ተቀራራቢ ወይም ተመጋጋቢ የምርት እና/ወይም የሙያ ግንኙነት ያላቸው አምራች ድርጅቶች እና/ወይም ባለሙያዎች የያዘ ማህበር ነው፡፡

8. “ማቀነባበር” ማለት በፋብሪካ ወይም በሃይል ምንጭ በሚንቀሳቀስ ማሽን ምርትን እሴት ጨምሮ ማምረት ነው፡፡

9. “ማዘጋጀት” ማለት በግብርና፣ በማዕድን ወይም በግንባታ ሥራ ምርትን እሴት ጨምሮ ማዘጋጀት ነው፡፡

10. በንግድና የዘርፍ ማህበራት ምክር ቤቶች ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 341/1995 ትርጓሜ የተሰጣቸው ቃላትና ሀረጎች በዚህ መመሪያ ተፈጻሚ ይሆናሉ፡፡

## 3. <u>የተፈፃሚነት ወሰን</u>

ይህ መመሪያ "የንግድና የዘርፍ ማኅበራት ምክር ቤቶች ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 341/1995 እና የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፑብሊክ አስፈፃሚ አካላትን ሥልጣንና ተግባር ለመወሰን የወጣ አዋጅ ቁጥር 691/2003 በማምረት ዘርፍና በሙያ በተደራጁና በሚደራጁ የዘርፍ ማኅበራት፣ የዘርፍ ማኅበራት ምክር ቤቶች እና የሙያ ማኅበራት ላይ ተፈጻሚነት ይኖረዋል፡፡

# ክፍል ሁለት
# የዘርፍ ማኅበራት እና የዘርፍ ማኅበራት ምክር ቤት ዓላማ፣ አመሠራረት፣ ድጋፍ አሰጣጥና ክትትል

## 4. <u>የዘርፍ ማኅበራትና የዘርፍ ማኅበራት ምክር ቤቶች አላማ</u>

በየደረጃቸው የሚቋቋሙ የዘርፍ ማኅበራትና የዘርፍ ማኅበራት ምክር ቤቶች የሚከተሉት ዓላማዎች ይኖራቸዋል፡፡

1. አምራቾች በየስራ ዘርፋቸው የሚደራጁበትንና የሚጠናከሩበትን ሁኔታ ማመቻቸት፣
2. በገጠርና በከተማ ዕደ ጥበባት አምራቾችን ማበረታታት፣
3. የአገሪቱ ምርቶች የጥራት ደረጃ ከፍ እንዲል አስፈላጊውን ድጋፍ መስጠት፣
4. የምርት መረጃዎችን መጠናቀርና ማሠራጨት፣
5. አባላት ዕውቀታቸውን፣ ሀብታቸውንና ጉልበታቸውን በማስተባበር በኢኮኖሚያዊ እንቅስቃሴዎች ውስጥ እንዲሳተፉ ማበረታታት፣
6. አባላት ጥቅማቸውን በጋራ ለማስጠበቅ እንዲችሉ ሁኔታዎችን ማመቻቸት፣
7. አባላት በየዘርፋቸው ያካበቱትን ዕውቀትና ልምድ አስመልክቶ መረጃዎችን የሚለዋወጡበትን መድረክ መፍጠር፣
8. የዘርፍ ማኅበራት በተለያዩ ጉዳዮች ላይ ከመንግስት ጋር የጋራ ውይይት የሚያደርጉበትን ሁኔታ ማመቻቸት፣
9. ሌሎች ተመሳሳይ ዓላማዎችን ያከናውናሉ፡፡

## 5. የዘርፍ ማኅበራት አመሠራረት

1. የዘርፍ ማኅበራት በየዘርፉ በግብርና ምርት ማምረትና ማቀነባበር፣ በፋብሪካ ምርት አምራችነት፣ የማዕድን ምርትና የግንባታ ሥራ እና በማንኛውም የማምረት ተግባር ላይ በተሠማሩ ድርጅቶች ባለቤቶች በወረዳ ወይም በክልል ወይም በአገር አቀፍ ደረጃ ሊመሠረቱ ወይም ሊቋቋሙ ይችላሉ፡፡

2. አምራች ድርጅቶች የተሠማሩበትን የማምረት ተግባር ዓይነትና የዘርፍ ማኅበራቱ እንዲኖራቸው ከሚፈልጉት አባላት ብዛት አንፃር በማገናዘብ፣ በዚህ መመሪያ ከተዘረዘሩት በተጨማሪ የሚቋቋሙ የዘርፍ ማኅበራትን እንደአስፈላጊነቱ ሚኒስቴሩ ሊወስን ይችላል፡፡

3. ባለ ብዙ ማኅበራት የመደራጀት ጥያቄ በሚያቀርቡበት ጊዜ የተሠማሩበትን ማምረት ተግባር ዓይነትና የዘርፍ ማኅበራቱ እንዲኖራቸው ከሚፈልጉት አባላት ብዛት አንፃር በማገናዘብ፣ ከሀገር አቀፍ የዘርፍ ማኅበራት ምክር ቤት ሥልጣንና ተግባር እና ከዚህ መመሪያ ጋር የማይቃረን ወይም የማይጋጭ መሆኑን በማጣራት እንደአስፈላጊነቱ ሚኒስቴሩ ሊወስን ይችላል፡፡

## 6. በወረዳ ደረጃ የሚደራጁ የዘርፍ ማኅበራት

በወረዳ ደረጃ የሚደራጁ የዘርፍ ማኅበራት የሚከተሉት ይሆናሉ

1. የቤት እንስሳት አርቢዎችና የእንስሳት ውጤት አምራቾች ማኅበር
2. የንብ አናቢዎች እና የማር አምራቾች ማኅበር
3. የቡና አጣቢዎችና አበጣሪዎች ማኅበር
4. የእህል ወፍጮ ባለቤቶች ማኅበር (አነስተኛ ወፍጮዎች)
5. የእንጨትና እንጨት ውጤቶች አምራቾች ማኅበር
6. የልብስና የሸራ ሰፊዎች ማኅበር (በአነስተኛና ጥቃቅን የሚገኙ አምራቾች)
7. የባልትናና ባህላዊ ምግብ ውጤቶች አምራቾች ማኅበር
8. የማስታወቂያና ህትመት አምራቾች ማኅበር

9. የአነስተኛ የግንባታ ዕቃዎች አምራቾች ማኅበር

10. የሽመና ውጤቶች፣ ሹራብና ምንጣፍ አምራቾች ማኅበር

11. የብረታ ብረት ውጤቶች አምራቾች ማኅበር (በአነስተኛና ጥቃቅን የሚገኙ ድርጅቶች)

12. የጌጣጌጥና ባህላዊ ጥበባት አምራቾች ማኅበር

13. የሸክላ ሥራዎች አምራቾች ማኅበር

14. የቆዳ ውጤቶች አምራቾች ማኅበር (በአነስተኛና ጥቃቅን የሚገኙ ድርጅቶች)

15. የእንጉዳይ ውጤቶች አምራቾች ማኅበር

16. የጥራጥሬ ቅባት እህሎች እና ቅመማቅመም አምራቾች ማኅበር

## 7. <u>በክልል ደረጃ የሚደራጁ የዘርፍ ማኅበራት</u>

በክልል ደረጃ የሚደራጁ የዘርፍ ማኅበራት የሚከተሉት ይሆናሉ

1. ኮሜርሻል የቡና አምራቾችና የቡና አቀነባባሪዎች ማኅበር
2. የዓሣ አምራቾች ማኅበር
3. ኮሜርሻል ማርና ሰም አምራቾች ማኅበር
4. ኮሜርሻል የወተትና የወተት ውጤቶች አምራቾች ማኅበር
5. ኮሜርሻል ቅባትና ጥራጥሬ ሰብል እህሎች አምራቾች ማኅበር
6. ኮሜርሻል የምግብ እህል አምራቾች ማኅበር
7. ኮሜርሻል የቅመማ ቅመም፣ ዕጸችና መዓዛማ ዘይቶች አብቃዮች ማኅበር
8. የደን ልማት አምራቾች ማኅበር
9. የእንጨትና እንጨት ውጤቶች አምራቾች ማኅበር
10. የምግብ ዘይት ውጤቶች አቀነባባሪዎች ማነበር
11. የባልትና ውጤት አምራቾች ማኅበር

## 8. <u>በአገር አቀፍ ደረጃ የሚደራጁ የዘርፍ ማኅበራት</u>

በአገር አቀፍ ደረጃ የሚደራጁ የዘርፍ ማኅበራት የሚከተሉት ይሆናሉ

1. የኢትዮጵያ የአትክልትና ፍራፍሬ አምራቾች ማኅበር
2. የኢትዮጵያ አበባ አምራቾችና ላኪዎች ማኅበር
3. የኢትዮጵያ የቡና አምራቾች አዘጋጅቶ ላኪዎች ማኅበር
4. የኢትዮጵያ የምርጥ ዘር አምራቾች ማኅበር
5. የኢትዮጵያ የዱቄትና የዱቄት ውጤቶች አምራቾች ማኅበር
6. የኢትዮጵያ አልሚ ምግብ አምራቾች ማኅበር
7. የኢትዮጵያ የቢራ አምራች ኢንዱስትሪዎች ማኅበር
8. የኢትዮጵያ የአልኮል መጠጦች አምራች ኢንዱስትሪዎች ማኅበር
9. የኢትዮጵያ የለስላሳና የታሸጉ ማዕድን ውኃ አምራች ኢንዱስትሪዎች ማኅበር
10. የኢትዮጵያ የአትክልትና ፍራፍሬ ማቀነባበሪያ አምራች ኢንዱስትሪዎች ማኅበር
11. የኢትዮጵያ የቤትና የቢሮ ዕቃዎች አምራች ኢንዱስትሪዎች ማኅበር
12. የኢትዮጵያ ቆዳ ኢንዱስትሪዎች ማኅበር
13. የኢትዮጵያ የጨርቃ ጨርቅና አልባሳት አምራች ኢንዱስትሪዎች ማኅበር
14. የኢትዮጵያ የስኳርና ጣፋጭ አምራች ኢንዱስትሪዎች ማኅበር
15. የኢትዮጵያ አታሚዎች ማኅበር
16. የኢትዮጵያ የመድኃኒትና የሕክምና መገልገያዎች አምራቾች ማኅበር
17. የኢትዮጵያ የኬሚካል ውጤቶች አምራቾች ማኅበር
18. የኢትዮጵያ ኤሌክትሮ መካኒካል፣ ኤሌክትሪካል እና ኤሌክትሮኒክስ ዕቃዎች አምራቾች ማኅበር

19. የኢትዮጵያ መሠረታዊ ብረታ ብረቶችና ኢንጂነሪንግ አምራቾች ማኅበር
20. የኢትዮጵያ ማሽነሪ እና የማሽነሪ ዕቃዎች አምራቾች ማኅበር
21. የኢትዮጵያ ጤናና ውበት መጠበቂያ አምራቾች ማኅበር
22. የኢትዮጵያ የጎማና ፕላስቲክ ውጤቶች አምራቾች ማኅበር
23. የኢትዮጵያ ፕላስቲክ፣ጎማና ዘይቶች እንደገና ሠሪዎች ማኅበር
24. የኢትዮጵያ ብርጭቆ፣ ጠርሙሶች፣መስታወትና የመስታወት ውጤቶች አምራቾች ማኅበር
25. የኢትዮጵያ ሴራሚክና የህንፃ ጡቦች አምራቾች ማኅበር
26. የኢትዮጵያ ሲሚንቶ አምራቾች ማኅበር
27. የኢትዮጵያ የእምነበረድና ቴራዞ አምራቾች ማኅበር
28. የኢትዮጵያ ሸክላ፣ ኖራና ሌሎች መለሰኛዎች አምራቾች ማኅበር
29. የኢትዮጵያ ብረታ ብረት ያልሆኑ የማዕድን ውጤቶች አምራቾች ማኅበር
30. የኢትዮጵያ የከበሩ ማዕድናት አምራቾች ማኅበር
31. የኢትዮጵያ የወረቀትና ወረቀት ውጤቶች አምራቾች ማኅበር
32. የኢትዮጵያ የማሸጊያ ምርት አምራቾች ማኅበር
33. የኢትዮጵያ አውቶሞቲቭ ኢንዱስትሪዎች ማኅበር
34. የኢትዮጵያ ሥጋ አምራቾችና ላኪዎች ማኅበር
35. የኢትዮጵያ የዶሮ ሥጋ አምራቾችና አቀናባሪዎች ማኅበር
36. የኢትዮጵያ የቁም እንስሳት አቅራቢዎችና ላኪዎች ማኅበር
37. የኢትዮጵያ ማርና ሠም አቀነባባሪዎችና ላኪዎች ማኅበር
38. የኢትዮጵያ የወተት ተዋፅኦ አምራች ኢንዱስትሪዎች ማኅበር
39. የኢትዮጵያ የቅባትና ጥራጥሬ እህሎች አዘጋጆችና ላኪዎች ማኅበር

40. የኢትዮጵያ የቅመማ ቅመም፣መዓዛማና ሐመልማላማ ዘይቶች አቀነባባሪዎችና ላኪዎች ማኅበር

41. የኢትዮጵያ የቡና ቆይዎችና ፈጭቶ አሻጊዎች ማኅበር

42. የኢትዮጵያ የሰሊጥ አቀነባባሪዎችና ላኪዎች ማኅበር

43. የኢትዮጵያ የምግብ ዘይት አምራች ኢንዱስትሪዎች ማኅበር

44. የኢትዮጵያ የእንስሳት መኖ ኢንዱስትሪ ማኅበር

45. የኢትዮጵያ የእንጉዳይ ውጤቶች አምራቾችና አቀነባባሪዎች ማኅበር

46. የኢትዮጵያ ታክሲ ደርሚ አምራች ማኅበር

47. የኢትዮጵያ ጥጥ አምራቾችና መዳመጫ ባለቤቶችና ላኪዎች ማኅበር

48. የኢትዮጵያ የጥልቅ ውኃ ጉድጓድ ቆፋሪዎች ማኅበር

49. የኢትዮጵያ የውኃ ነክ ስራዎች ግንባታ ተቋራጮች ማኅበር

50. የኢትዮጵያ የጨው ምርት አምራቾች ማኅበር

51. የኢትዮጵያ የታሸጉ የምንጭ ውኃ አምራቾች ማኅበር

52. የኢትዮጵያ ማዕድናትና ተዛማጅ ውጤቶች አምራቾች ማኅበር (የይዘት ለውጥ ሳያስከትሉ የማዕድን ውጤቶች፤ ማለትም እንደ አሸዋ፣ ብሎኬትና የመሣሰሉትን የሚያመርቱ)፡፡

## 9. የዘርፍ ማኅበራት ምክር ቤቶች አመሠራረትና ውክልና

1. በወረዳ ደረጃ የተቋቋሙ የዘርፍ ማኅበራት የየወረዳውን የዘርፍ ማኅበራት ምክር ቤቶች ያደራጃሉ፤

2. በየወረዳዎች የተቋቋሙ የዘርፍ ማኅበራት ምክር ቤቶችና በክልል ደረጃ የተደራጁ የዘርፍ ማኅበራት የየክልሉን የዘርፍ ማኅበራት ምክር ቤቶች ያደራጃሉ፣

3. በየክልሉ የተቋቋሙ የዘርፍ ማኅበራት ምክር ቤቶችና በአገር አቀፍ ደረጃ የተደራጁ የዘርፍ ማኅበራት አንድ አገር አቀፍ የዘርፍ ማኅበራት ምክር ቤት ያደራጃሉ፡፡

## 10. የዘርፍ ማኅበራትና የዘርፍ ማኅበራት ምክር ቤቶች ምዝገባና የሕጋዊ ሰውነት ማረጋገጫ አሰጣጥ

1. በአገር አቀፍ ደረጃ የተደራጁ የዘርፍ ማኅበራትና የዘርፍ ማኅበራት ምክር ቤቶች አስፈላጊውን ሁኔታ ሲያሟሉና የመመዝገቢያ ክፍያ ሲፈጽሙ በሚኒስቴሩ ይመዘገባሉ፣ ለዚሁም የህጋዊ ሰውነት ማረጋገጫ የምሥክር ወረቀት ያገኛሉ፣

2. በክልል እና በወረዳ የተደራጁ የዘርፍ ማኅበራትና የዘርፍ ማኅበራት ምክር ቤቶች አስፈላጊውን ሁኔታ ሲያሟሉና የመመዝገቢያ ክፍያ ሲፈጽሙ በሚመለከተው የክልል ወይም የወረዳ ኢንዱስትሪ ልማት ቢሮዎች/ጽ/ቤቶች ይመዘገባሉ፣ ለዚሁም የህጋዊ ሰውነት ማረጋገጫ የምሥክር ወረቀት ያገኛሉ፣

3. ሚኒስቴሩ ወይም በተዋረድ ያሉ የክልል ወይም የወረዳ ቢሮዎች/ጽ/ቤቶች ማመልከቻ እና አስፈላጊው መረጃ ተሟልቶ ሲቀርብላቸው በ30 ቀን ውስጥ አመልካቾቹን በዘርፍ ማኅበርነት ወይም በዘርፍ ማኅበር ምክር ቤትነት በመመዝገብ የህጋዊ ሰውነት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ይሰጣሉ።

## 11. የዘርፍ ማኅበራትና የዘርፍ ማኅበራት ምክር ቤቶች አባል ለመሆን መሟላት ያለባቸው መመዘኛዎች ወይም ሁኔታዎች

1. ማንኛውም የዋና ምዝገባ ማረጋገጫ የምስክር ወረቀትና የንግድ ሥራ ፈቃድ የሚያቀርብ አምራች ተቋም የዘርፍ ማኅበር አባል መሆን ይችላል፣

2. ማንኛውም የምዝገባና የዕውቅና ምስክር ወረቀት የሚያቀርብ ዘርፍ ማኅበር በወረዳ ወይም በክልል ወይም በአገር አቀፍ ደረጃ የሚቋቋሙ ምክር ቤቶች አባል መሆን ይችላል፣

3. አምራች ድርጅቶች በግል ደረጃ የዘርፍ ማኅበራት ምክር ቤቶች አባል ሊሆኑ አይችሉም።

## 12. የዘርፍ ማኅበራትና የዘርፍ ማኅበራት ምክር ቤቶች ድጋፍና ክትትል

1. የዘርፍ ማኅበራት ምክር ቤቶች የንግድና የዘርፍ ማህበራት ምክር ቤቶች ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 341/1995 ላይ የተሰጣቸውን ሥልጣንና ተግባር እና የዘርፍ ማህበራት በመተዳደሪያ ደንባቸው ላይ ባስቀመጡት የማኅበሩን ዓላማ እንዲወጡ በሚኒስቴሩ ወይም በተዋረድ ባሉ በክልል ወይም በወረዳ ቢሮዎች ወይም ጽ/ቤቶች ድጋፍና ክትትል ይደረጋል፣

2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 በተገለጸው መሠረት ዓላማቸውን መወጣታቸውን የሚገልጽ ሪፖርትና እውቅና ባለው የሂሳብ ባለሙያ የተረጋገጠ የኦዲት ሪፖርት የበጀት ዓመቱ በተጠናቀቀ በ3 ወር ጊዜ ውስጥ ለሚኒስቴሩ ወይም በተዋረድ ባሉ የክልል ወይም የወረዳ ቢሮዎች/ጽ/ቤቶች ማቅረብ አለበት፣

## 13. <u>ስለፈቃድ እድሳት</u>

የማኀበሩ ዓመታዊ አፈጻጸምና እውቅና ባለው የሂሳብ ባለሙያ የተረጋገጠ የኦዲት ሪፖርት የተሟሉ መሆናቸውና የእድሳት ክፍያ መፈጸሙ ሲረጋገጥ የእያንዳንዱ የዘርፍ ማኅበር እና የዘርፍ ማኅበራት ምክር ቤት ፈቃድ በየሁለት ዓመቱ መታደስ ይኖርበታል፣

## 14. <u>ስለ ፈቃድ ዕገዳና ስረዛ</u>

ማናቸውም የዘርፍ ማኅበር እና የዘርፍ ማኅበራት ምክር ቤት፣

1. በአንቀጽ 13 መሠረት ዓመታዊ የሥራ ክንውን እና የኦዲት ሪፖርቶችን በጀት ዓመቱ በተጠናቀቀ በ3 ወር ጊዜ ውስጥ ካላቀረበ ወይም ፈቃዱን ካላሳደሰ ፈቃዱ ይታገዳል፤
2. የተመዘገበው በማታለል ወይም በማጭበርበር ከሆነ ወይም የተቋቋመበትን አላማ ወይም የሚፈለግበትን አገልግሎት የማይሰጥ ሆኖ ከተገኘ ፈቃዱ ይሠረዛል።

# ክፍል ሦስት
# የሙያ ማኅበራት ዓላማ ፣ አመሠራረት፣ ድጋፍ አስጣጥና ክትትል

## 15. <u>የሙያ ማኅበራት ዓላማ</u>

የሙያ ማኀበራት የሚከተሉት አላማዎች ይኖራቸዋል።

1. የአገሪቱ ምርቶች የጥራት ደረጃ ከፍ እንዲል አስፈላጊውን ድጋፍ መስጠት፣
2. አዳዲስ የአመራረት ቴክኖሎጂ መረጃዎችን ማጠናቀርና ማሠራጨት፣
3. አባላት ዕውቀታቸውን፣ ሀብታቸውንና ጉልበታቸውን በማስተባበር በኢኮኖሚያዊ እንቅስቃሴዎች ውስጥ እንዲሳተፉ ማበረታታት፣
4. ከአገር ውስጥም ሆነ ከውጪ ጠቃሚ የሆኑ ልምዶችና መረጃዎችን በማሰባሰብ መንግስት ለሚተገብራቸው ፖሊሲዎችና እስትራቴጂዎች ጠቃሚ መረጃዎችን መስጠት

5. አባላት በየዘርፋቸው ያካበቱትን ዕውቀትና ልምድ አስመልክቶ መረጃዎችን የሚለዋወጡበትን መድረክ መፍጠር፣
6. የሙያ ማኅበራት በተለያዩ ጉዳዮች ላይ ከመንግስት ጋር የጋራ ውይይት የሚያደርጉበትን ሁኔታ ማመቻቸት፣
7. ሌሎች ተመሳሳይ ዓላማዎችን ያከናውናሉ፡፡

## 16. <u>የሙያ ማኅበራት አመሠራረት</u>

1. የሙያ ማኅበራት በሕግ በተፈቀደው አኳኋን ሊመሠረቱ ይችላሉ፤
2. ከተመሳሳይ ሙያ የተውጣጡ ሰዎች ወይም ባለሙያዎች የሙያ ማኅበር ሊመሠርቱ ይችላሉ፤
3. ሚኒስቴሩ አምራች ድርጅቶች የተሠማሩበትን የሙያ ዓይነትና የሙያ ማኅበራቱ እንዲኖራቸው ከሚፈልጉት አባላት ብዛት አንፃር በማገናዘብ በዚህ መመሪያ ከተዘረዘሩት በተጨማሪ የሚቋቋሙ የሙያ ማኅበራትን እንደአስፈላጊነቱ ሊወስን ይችላል፡፡
4. በሚኒስቴሩ የሚመሠረቱ የሙያ ማኅበራት የሚከተሉት ይሆናሉ፣

ሀ.የኢትዮጵያ የኬሚስትሪ ባለሙያዎች ማኅበር

ለ.የኢትዮጵያ የኬሚካል ኢንጅነሮች ማኅበር

ሐ.የኢትዮጵያ የኢንዱስትሪዎች ዲዛይንና ኮሚሽን ባለሙያዎች ማኅበር

መ.የኢትዮጵያ የምግብ አማካሪ ባለሙያዎች ማኅበር

ሠ.የኢትዮጵያ የእንስሳት ሐኪሞች ማኅበር

ረ.የኢትዮጵያ የሰብል ሳይንስ ባለሙያዎች ማኅበር

ሰ.የኢትዮጵያ የእንስሳት ሀብት ልማት ባለሙያዎች ማኅበር

ሸ.የኢትዮጵያ የግብርና ባለሙያዎች ማኅበር

ቀ.የኢትዮጵያ የግብርና ኢኮኖሚክስ ማኅበር

በ.የኢትዮጵያ የቅመማ ቅመም፣ዕፆችና መዓዛማ ዘይቶች ባለሙያዎች ማኅበር

ተ.የኢትዮጵያ ሲቪል መሐንዲሶች ማኅበር

ቸ.የኢትዮጵያ መካኒካል መሐንዲሶች ማኅበር

ኀ.የኢትዮጵያ ቀያሽ ባለሙያዎች ማኅበር

ነ.የኢትዮጵያ አርክቴክቶች ማኅበር

ኘ.የኢትዮጵያ ኤሌክትሪካል መሐንዲሶች ማኅበር

አ.የኢትዮጵያ ምድር ባቡር መሐንዲሶች ማኅበር

ከ.የኢትዮጵያ የጨርቃ ጨርቅ መሐንዲሶች ማኅበር

ኸ.የኢትዮጵያ የሆርቲካልቸራል ባለሙያዎች ማኅበር

ወ.የኢትዮጵያ ስነ ሕይወት ባለሙያዎች ማኅበር

ዐ.የኢትዮጵያ ኢንዱስትሪያል መሐንዲሶች ማኅበር

ዘ.የኢትዮጵያ የንብ አናቢ ባለሙያዎች ማኅበር

## 17. የሙያ ማኅበራት ምዝገባ፣ ህጋዊ ሰውነት አሠጣጥ፣ ድጋፍና ክትትል

1. የሙያ ማኅበራቱ በአንቀጽ 20 በተገለጸው መሠረት አስፈላጊውን ሁኔታዎች ሲያሟሉና የመመዝገቢያ ክፍያ ሲፈጽሙ በሚኒስቴሩ ይመዘገባሉ፣ ለዚሁም ህጋዊ የሰውነት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ያገኛሉ፣

2. ሚኒስቴሩ ማመልከቻ እና መረጃ ተሟልቶ ሲቀርብለት በ30 ቀናት ውስጥ አመልካቾቹን በሙያ ማኅበርነት በመመዝገብ የህጋዊ ሰውነት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ይሰጣል፣

3. ሚኒስቴሩ የሙያ ማኅበራትን የሥራ ክንዋኔ ክትትል በማድረግ ድጋፍ ያደርጋል፣

4. እያንዳንዱ የሙያ ማኅበር ዓመታዊ የሥራ ክንዋኔ ሪፖርት እና በሂሳብ ባለሙያ የተረጋገጠ የኦዲት ሪፖርት በማዘጋጀት በጀት ዓመቱ በተጠናቀቀ በ3 ወር ጊዜ ለሚኒስቴሩ ማቅረብ ይኖርበታል።

## 18. ስለፈቃድ እድሳት፣

የማኅበሩ ዓመታዊ ክንውንና እውቅና ባለው የሂሳብ ባለሙያ የተረጋገጠ የኦዲት ሪፖርት የተሟሉ መሆናቸውና የእድሳት ክፍያ መፈጸሙ ሲረጋገጥ የእያንዳንዱ የሙያ ማኅበራቱ ፈቃድ በየሁለት ዓመቱ መታደስ ይኖርበታል፣

## 19. ስለፈቃድ ዕገዳና ስረዛ

ማንኛውም የሙያ ማኅበር፣

1. በአንቀጽ 18 መሠረት ዓመታዊ የሥራ ክንውን እና የኦዲት ሪፖርቶችን በጀት ዓመቱ በተጠናቀቀ በ3 ወር ጊዜ ውስጥ ካላቀረበ ወይም ፈቃዱን ካላሳደሰ ፈቃዱ ይታገዳል፣

2. የተመዘገበው በማታለል ወይም በማጭበርበር ከሆነ ወይም የተቋቋመበትን አላማ ወይም የሚፈለግበትን አገልግሎት የማይሰጥ ሆኖ ከተገኘ ፈቃዱ ይሠረዛል፡፡

# ክፍል አራት

## ማኅበራቱ እና የማኅበራት ምክር ቤቱ ምዝገባና ፈቃድ ለማድረግ መሟላት ስለሚገባቸው መስፈርቶች፣ የአገልግሎት ዘመንና የክፍያ መጠን

## 20. የዘርፍ ፣የሙያ ማኅበራቱ እና የዘርፍ ማኅበራት ምክር ቤቶቹ ምዝገባና ፈቃድ ለማግኘት መሟላት ስለሚገባቸው መስፈርቶች

1. በሕግ በተፈቀደው አኳኋን የተደራጁ መሆኑን በሚኒስቴሩ ወይም በተዋረድ ባሉ የክልል ወይም የወረዳ ቢሮዎች/ጽ/ቤቶች ሲረጋገጥ፣

2. ሁሉም የማኅበሩ አባላት በየገጽ የፈረሙበት ሦስት ኦርጂናል ቅጂ የማኅበሩን የመመስረቻ ፅሁፍ፣ መተዳደሪያ ደንብና የሥራ አስፈጻሚ አካላት ምርጫ ቃለ ጉባዔ እና
3. በሚኒስቴሩ በተዘጋጀው ቅጽ ሞልተው ከማመልከቻ ጋር ሲያቀርቡ በሚኒስቴሩ ወይም በተዋረድ ባሉ የክልል ወይም የወረዳ ቢሮዎች ወይም ጽ/ቤቶች የሚመዘገቡና የህጋዊ ሰውነትም ፈቃድ የሚያገኙ ይሆናል፡፡

## 21. <u>የዘርፍ ፣ የሙያ ማኅበራቱ እና የዘርፍ ማኅበራት ምክር ቤቶቹ ሕጋዊ ሰውነት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት አገልግሎት ዘመንና ክፍያ</u>

1. በዘርፍ ፣ በሙያ ማኅበርነት ወይም በዘርፍ ማኅበር ምክር ቤትነት ሕጋዊ የምስክር ወረቀት ለማውጣት ለአዲስ ወይም ለእድሳት ብር 100 (አንድ መቶ) የአገልግሎት ክፍያ ለሚኒስቴሩ ወይም በተዋረድ ባሉ የክልል ወይም የወረዳ ቢሮዎች ወይም ጽ/ቤቶች መክፈል ይኖርበታል፣

2. ሕጋዊ የምስክር ወረቀት ከተሰጠበት ወይም ከታደሰበት ጊዜ ጀምሮ ለሁለት ዓመት ብቻ ያገለግላል፡፡

# ክፍል አምስት
# ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

## 22. <u>መመሪያውን የማሻሻል ወይም የመሻር ሥልጣን</u>

አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ሚኒስቴሩ ይህን መመሪያ በማንኛውም ጊዜ ማሻሻል ወይም መሻር ይችላል፡፡

## 23. <u>የተሻሩ መመሪያዎች</u>

በቀድሞ የንግድና ኢንዱስትሪ ሚኒስቴር የንግድና የዘርፍ ማኅበራት ምክር ቤቶችን ለማቋቋም የወጣውን አዋጅ ቁጥር 341/1995 ለማስፈጸም የወጣው መመሪያ ኢንዱስትሪን በሚመለከት በዚህ መመሪያ ተሽሯል፡፡

## 24. <u>የመሸጋገሪያ ድንጋጌዎች</u>

1. ከዚህ መመሪያ ጋር የሚጋጭ ሁኔታ ካልተነሳ በስተቀር ቀደም ሲል የተመዘገቡ የዘርፍ፣ የሙያ ማኅበራቱ እና የዘርፍ ማኅበራት ምክር ቤቶቹ የህጋዊ ሰውነት ማረጋገጫቸውን በማደስ ተግባራቸውን ሊቀጥሉ ይችላሉ፡፡

2. ከላይ በንዑስ አንቀጽ 1 በተገለጸው መሰረት  ቀደም ሲል የተመዘገቡ የዘርፍ፣ የሙያ ማኅበራቱ እና የዘርፍ ማኅበራት ምክር ቤቶቹ ይህ መመሪያ ሥራ ላይ ከዋለበት ቀን ጀምሮ በ6 ወር ጊዜ ውስጥ ቀርበው ፈቃዳቸውን ማሳደስ ይኖርባቸዋል፡፡ ይህንኑ የሚመለከታቸው ቢሮዎች/ጽ/ቤቶች ለማኅበራቱ እና ለምክር ቤቶቹ ያሳውቃሉ፡፡

## 25. ስለ ቅሬታ አቀራረብና አፈታት ሥርዓት

1. ማንኛውም የዘርፍ ማኅበር ወይም የዘርፍ ማኅበራት ምክር ቤት ወይም የሙያ ማኅበር እገዳንና ስረዛን በተመለከተ ቅሬታ ካለው እገዳው ወይም ስረዛው ከተደረገበት ጊዜ ጀምሮ ባለው 3 ወር ጊዜ ውስጥ በተዋረድ ባለው ለሚመለከተው አካል በማመልከቻ ማቅረብ ይኖርበታል፣

2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 መሠረት ሚኒስቴሩ ወይም በተዋረድ ያሉ የክልል ወይም የወረዳ ቢሮዎች/ጽ/ቤቶች ቅሬታው ከቀረበበት ጊዜ ጀምሮ ባለው አንድ ወር ጊዜ ውስጥ ውሳኔውን በጽሁፍ ማሳወቅ ይኖርበታል፡፡

## 26. መመሪያው የሚፀናበት ጊዜ

ይህ መመሪያ ከሚያዚያ 15 ቀን 2007 ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

አዲስ አበባ ሚያዚያ 15 ቀን 2007 ዓ.ም

አህመድ አብተው

የኢንዱስትሪ  ሚኒስትር